# እዘክሬ ድንግል

የግብጽ በረሐ ራብ ውኃ ጥሙ፣
የስጋቱ መንገድ መከራ ድካሙ፣
ገና ሳይታሰብ ገና ሳይጀመር፣
የድንግል ማርያም የስደትዋ ነገር፣
በሌሊት ሊናገር የሸሸትዋን ጉዳይ፣
የእግዚአብሔር መልአክ ለዮሴፍ ሳይታይ፣
ከአረጋዊው ስምዖን ድንግል ሰምታ ነበር፣
በነፍስሽ ጦር ያልፋል እያለ ሲናገር።

የስምዖን ትንቢት ፍጻሜው ጀመረ፣
ስደት ድንገት መጣ ዮሴፍ ተበሰረ።



ልጅዋ እንዳይገደል ድንግል ተጨነቀች፣
ወልድን ተሸክማ ስደትን ቀመሰች።
የዚያ ዘመን ችግር እንዴት እንደነበር፣
የሕፃናቱን ሞት የሔሮድስን ነገር፣
ድንግል የአብ ሙሽራ እሙ ለክርስቶስ፣
ለሊቀ ጳጳሳት ለአባ ጢሞቴዎስ፣
ስጋቷን ፍርሐቷን ጭንቅና ኀዘንዋን፣
ድንግል በመገለጥ አሰማች ዜናዋን።

በስደት መውጣቷን ከአገር ከመንደርዋ፣
በውል አስረዳችው ማርያም ድንግሊትዋ።

በሰማይ ሰልፍ ሆኖ የረታው ሚካኤል፣
የቀደመው እባብ አሳቹ ሳጥናኤል፣



በጽኑ ኃይልና በሚያስፈራ ቁጣ፣
ሰውን ዳግም ሊያስት ወደ ምድር መጣ
ማደሪያ ሲፈልግ በባሕር በምድሩ፣
ሄሮድስን አገኘው ዲያብሎስ ለግብሩ።
ኢየሱስ ክርስቶስ የተፈተንክበት፣
ገዳመ ቆሮንቶስ ድል የነሣህበት፣
የሥልጣን ጥያቄ ሔሮድስ ደርሶበት፣
ፍርድን አበላሸ ተፈጸመ ስህተት።
ዕድሜ ልኩን ላይኖር ሔሮድስ በስልጣን፣
አንገቱን አስቀላው ያንን ሁሉ ሕፃን።
አንቺ ቤተልሄም ኀዘን ደረሰብሽ፥
ገና ጡት ሳይጠግቡ ሕፃናት ሞቱብሽ።
ሁለት ዓመት እና ከዛ በታች ያሉ፣
በጨካኙ ሔሮድስ በግፍ ተገደሉ።

ቀድሞ በኤርምያስ ሲነገር የቆየው፣
የሕፃናቱ ሞት በራእይ የታየው፣
በእርስዋ ተፈጽሞ መጽናናት ከበዳት፣
ራሔል አነባች ልጆች ሞተውባት።

እንዴት አያሳዝን እንዴት አያስፈራ፣
ሕፃን ይገደላል ብሎ እየተወራ።
አረጋዊው ስምኦን እንዳነጋገረሽ፣
በነፍስሽ ጦር አልፏል ስጋቱ ጀመረሽ።



ንግሥት በአህያ ንጉሥ ተሸክመሽ፣
የገሊላን ምድር አገርሽን ትተሽ፣
ለማይቀረው መንገድ ለስደት ተነሣሽ፡
በግብፅ በረሐ ውኃ እየተጠማሽ።
ዝናብ የታየብሽ ትንሿ ደመና፣
አንቲ መሶበ ወርቅ ውስጥሽ ያለ መና።



በሰማይ በክብር በቀኝ በኩል ቢያይሽ፡
ወትቀውም ንግሥት ብሎ ተቀኘልሽ።

እንደ ልቤ የሚል ስም ከላይ የተሰጠው፡
ከእረኝነት መርጦ ንጉሥ ያደረገው፡
በፀጋ ተመልተሽ ቢመለከት ከብረሽ፡
በግርማ በሞገስ ወርቅ ተጎናጽፈሽ፡

አድማስ የሚያሻግር ጭኖ በደመና፣
አእምሮ የሚሰውር የሚሰርቅ ሕሊና፣
የስምዋ ስጦታ የእግዚአብሔር ነውና፣
ዕለት ዕለት አዲስ የማርያም ምስጋና።
ቀድማ የነበረች በሐሳበ ሥላሴ፣
ቢነገር አያልቅም የድንግል ውዳሴ።
የዳዊት መወድስ የኢሳይያስ ስብከት፣
የካህናት ዜማ የሊቃውንት እውቀት፣
የሰው ልጆች ተስፋ የአዳም የስብከት ቃል፣
የነቢያት ምሥጢር የሲና ሐመልማል፣
የሕዝቅኤል ራእይ የነቢያት ትንቢት፡
ቅኔው ለሰሎሞን መዝሙሩ ለዳዊት።
ተሰምቶ አይጠገብ ውዳሴሽ መብዛቱ፣
ለአባ ሕርያቆስ አንቺ ነሽ ድርሰቱ።

እናታችን ማርያም ጥዑመ ስም ያለሽ፣
ጥዑመ ስም ያለው ክርስቶስን ወልደሽ፣
ዓለም ይባረካል ይኸው እስከ ዛሬ፣
መድኃኒት ነውና ከአንቺ የወጣው ፍሬ።

አባ ሕርያቆስ ውዳሴሽ በዝቶለት፣
የምስጋናሽ ነገር ምሥጢር ተገልጦለት፣
የክብርሽን ነገር በአድናቆት በማየት፣
ይመሰክር ጀመር በጣፈጠ አንደበት።
እግሩ ከምድር ሳይለቅ ሐሳብ አመጠቀው፣
በደመና ጭኖ የኋሊት ወሰደው።
ያሬድ በዝማሬው ንዑድ ክቡር ያለሽ፣
ኪዳነ - ምሕረት የገነት ቁልፍ ነሽ።

**ወስብሐት ለእግዚአብሔር።**
**አብርሃም ሰሎሞን።**
ABRAHAM SOLOMON